# ሰባተኛው ንጉሥ አፄ ክህደቱና ኢትዮጵያዊው እራስፑቲን

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል የተዘጋጀ

ጥር 5 ቀን 2014 ዓም(13-01-2022)

የውሸትና የክህደት አጼ የሆነው አብይ አህመድ አሊ ገና ከጧቱ ወደሥልጣን ወንበር ላይ ሲመጣ ውሸቱን ሀ ብሎ የጀመረው በሰባት ዓመቴ እናቴ ሰባተኛው ንጉሥ ትሆናለህ ብላኝ ነበር፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የንጉሥነት ስሜት ተጫጭኖኝ ጓደኞቼ እንኳን ከጎኔ ቆመው ፎቶ እንዳይነሱ እከለክላቸው ነበር፣ያ የእናቴ ትንቢት ከሰላሳ አምስት ዓመት በኋላ ተከስቶ ይኸው መሪ ለመሆን በቃሁ በማለት በሕዝብ ፊት በፓርላማው ወለል ላይ ሳያፍር ተናገረ።ያ ንግግሩ ምን ያህል ለሥልጣን እንዳደረና ጭንቅላቱን እንዳሳበጠው የሚያመልከት የቅርብ ጊዜ ትዝታ ከመሆኑም ባለፈ አሁን ለሚያሳዬው ቁሳራዊ ማገ አለብኝነት መንደርደሪያ ሆኗል።

ይኸው ጉደኛ በዚህም በዚያም ብሎ የአመራሩን ቦታ ከጨበጠ ወዲህ ብዙ ውሸቶችንና ክህደቶችን ፈጽሟል።በአድር ባይ ኮልኮሌዎቹ ታጅቦ አሁንም የለመደ ውሸቱንና ክህደቱን አላቆመም፤እንደውም ካፈርኩ አይመልሰኝ ብሎ ሽምጥ እዬጋለበበት ነው።በዚህ ክህደትና ውሸት በተቀላቀለበት ማንነቱ ና አመራሩ አገርና ሕዝብ ለጉዳትና ለውርደት ተጋልጠዋል።ያንን ደካማና የወንጀል ሥራ እንደ ሞግዚትና ካባ ሆነው የሚሸፋፍኑ ብዙ አድር ባዮችም ከጎኑ አልጠፉም።ጥፋቱን፣ ጨካኝና የሥልጣን እብድነቱን በመካድ ፣ የፍቅር፣ የይቅርባይነት፣የደግነት፣የአስተዋይነት፣የአገር ወዳድነት፣የጀግንነት፣የፈርሃ እግዚአብሔር ተምሳሌት አድርገው ሕዝብን በማሞኘት ላይ ተሰማርተዋል።ከነዚህ አንዱ ሃይማኖትንና ፖለቲካን አዳቅሎ የሕዝብን እይታ ለመለወጥ የሚዳክረው አንዱ ዳንኤል ክብረት የተባለው የኢትዮጵያ ራስፑቲን ነው።

ስለራስ ፑቲን ትንሽ እንንገራችሁና ከዳንኤል ክብረት ጋር ያለውን ምስስል እናሳያችሁ።ምናልባት የፑቲን ስም ሲነሳ አሁን በሩስያ ሥልጣን ላይ የተቀመጡትን ቪላድሚር ፑቲንን ታስቡ ይሆናል፣ ግን አይደለም፤ከመቶ አምስት ዓመት በፊት የሞተውን በሩስያ የቤተመንግሥት አድራጊ ፈጣሪ የነበረውን መነኩሴ ማለታችን ነው።

ግሪጎሪ ጀፊሞቪች ራስፑቲን ይባላል።ይህ እረጅምና ቀጭን ሰው በሩሲያ ሳይቤሪያ በተባለው በረዷማ ግዛት በፈረንጆቹ አቆጣጠር በጃንዋሪ 21 ቀን 1869 ተወልዶ በ30 ዲሴምበር 1916 የተገደለ ሲሆን በተወለደበት ቦታ የቤተሰብ መሪ የነበረና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከኖ ቤተሰቡን በትኖ ወደ መንግሥታዊ መናኸሪያ ወደነበረችው ሴንፒትስበርግ ከተማ የዘለቀ መነኩሴ አይሉት ጠንቋይ፣ጠንቋይ አይሉት አወናባጅ ቤተመንግሥቱን ጥሶ ለመግባት የቻለ ሰው ነበር።በተንኮልና በመተት፣እንዲሁም በሃይማኖታዊ የማሳመን ድፍረቱ በወቅቱ የራሽያ ንጉስ( ዛር)በነበረው ኒኮላ ሁለተኛ ዙፋን የቅርብ የችሎትና የፖለቲካ አማካሪ ለመሆን ከሙብቃቱም በላይ ከንግሥቲቱ ጋር የቀረበ ወዳጅነት እንደነበረውም ይነገራል።በዚህ ሰው ምክር ንጉስ ኒኮላ ብዙ ስህተቶችን እንደፈጸመና ለውድቀቱም ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።ታዲያ በዚያው ሰው ምክር የተነዳው ኒኮላ ሁለተኛ የዛር ስርወመንግሥት የመጨረሻው ሆነ፤ራስፑቲንም የተንኮሉ ሁሉ ጳጳስ ተደርጎ በአማጽያን እጅ ተገሎ አስከሬኑ ወንዝ ውስጥ ተጥሎ ተገኘ።

ይህንን እንደቀዳማዊ ራስፑቲን ወስደን በአገራችን የነቡሩና ያሉትን  ዳግማዊና  ሳልሳዊ እራስ ፑቲኖቹን ስናነሳ፣በንጉሥ ሃይለስላሴ ዙፋን ዙሪያ የነበሩት መነኩሴ ፣የንጉሡ ነፍስ አባትና ንብረት ሃላፊ ወይም በጅሮንድ የነበሩት አባ ሃና አንዱ ናቸው።አባ ሃና ለከፋቱም፣ለንፉግነቱም የንጉሡ አማካሪ ናቸው ተብለው የሚወቀሱና የሚጠሉ ነበሩ።በታህሳሱ 1953 ዓም ወታደራዊ እንቅስቃሴ ከተገደሉት ባለሥልጣኖች መሃል አንዱ ነበሩ።አሁን በእኛ ዘመን፣ ባለው የጎሰኞች ስርዓተመንግሥት ውስጥ በመሪነት ቦታ ለተቀመጠው ለክህደቱ ቁንጮ፣ለሰባተኛው ንጉሥ፣ ለአብይ አህመድ መካሪና አስተማሪ ብሎም ተከላካይ ሆኖ የተቀመጠው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በሳልሳዊ እራስፑቲንነት ቢጠራ ስህተት አይመስለንም።እሱም እንዳለፉት ሁለት ራስፑቲኖች የዙፋኑ አማካሪና አወዳሽ ብሎም የጥፋት አባሽ በመሆን በማገልገል ላይ ነው።

ያለፉትን የአብይ አህመድን ብዙ ክህደቶችና ውሸቶችን ሕዝቡ እንዳያውቅ በመሸፋፈንና ሌላ ትርጉም በመስጠት መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ሽፋን በመስጠት ሕዝቡን በማማለል ሳልሳዊ ራስፑቲን ዳንኤል ክብረት  ትልቅ ሚና ተጫውቷል፤እዬተጫወተም ነው።ሌላውን ትተን የሰሞኑን ትልቅ የአብይ አህመድን ክህደት እንደ ብስለትና ወደ ሌላ ትልቅ ድል የሚመራ ውሳኔ አድርጎ ማቅረቡ ምን ያህል ደፋር፣ ይሉኝታ ቢስና አድርባይ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

አብይ አህመድ ለሥልጣኑ ሲል ከወያኔ ጋር በከፈተው ጦርነት ብዙ ሽህ ዜጎች ካለቁ ፣ከቆሰሉና ከተፈናቀሉ፣ብዙ የሃገር ሃብትና ንብረት ከጋዬ፣ከተዘረፈ፣ በኋላ ፣ወንጀለኞቹን ለፍርድ ለማቅረብ መስዋእትነት ተከፍሎ የተያዙትን ጥቂት የጥፋት ሃይሎቹን ቁንጮዎች  በነጻ የመለቀቁ ክህደት ሲከሰት የተነሳውን የሕዝብ ተቃውሞ ለማለዘብ የመጀመሪያውና ግንባር ቀደም ሆኖ የወጣው ይኸው ጉደኛ ዳንኤል ክብረት ወይም ሳልሳዊ እራስፑቲን ነው።የእስረኞቹ መለቀቅ አሮጌና የማይረባ እቃን ሸጦ አዲስና ጠቃሚ ዕቃን ለመግዛት የተደረገ አትራፊ ንግድ ነው ብሎ አረፈው።የእሱ አሮጌ ዕቃ ስብሃት ነጋ ሲሆን አዲስና ጠቃሚው ዕቃ ደግሞ ጁዋር ሙሃመድ ሊሆን እንደሚችል ከንግድ ዝውውሩ ያዬነው ውጤት ያረጋግጥልናል።ለሳልሳዊ እራስፑቲን ለዳንኤል ክብረት በመቶ ሽህ የሚቆጠረው የንጹሃን ፣የሃጻን፣የአዛውንት፣የሴቶች፣ የአገር ደህንነት አስከባሪ ዜጎች ህይወት መጥፋት፣እራሱ ያደገባት ቤተክርስቲያን መውደምን ከመጤፍ አይቆጠርም፤ለሱ የተከፈሉ  እርካሽ ሸቀጦች ናቸው።ለውዱ ዋጋ ፣ ለኦነግና ለወያኔ ዳግም መንሰራራት የተከፈሉ እርካሽና መናኛ መስዋእት ናቸው ማለቱን ልብ ልንለው ይገባል።።የነገው ውድ ዋጋና  የሚከፈል እርካሽ ደግሞ ምን እንደሚሆን  መገመት አያቅትም።ይህ የአገርን ክብር አሳልፎ የተሰጠበት ውድ ዋጋ ተብሎ ሊቀርብ የሚችለው  ከአሜሪካኖች የሚገኘው ብድርና እርዳታ? ወይም የታጣው የጎዋ የነጻ ገበያ መብት ሊሆን ይችላል።የትኛው ክብር እንዳለው መፍረዱ የሁሉም አገር ወዳድ ድርሻ ነው።የአገር ክብር አንድነትና ነጻነት ወይንስ ለድሃው ሕዝብ የማይተርፈው፣ባለሥልጣናትና አጃቢዎቻቸው ለሚከፋፈሉት በዕዳ ለተጠቀለለ ብድርና ከቀረጽ ነጻ የሆነ የገባያ ዝውውር?

አጼ ክደቱ አብይ አህመድ፣አሁንም ከውሸት ማማ ላይ አልወረደም፣የሚያስንቁ ዉሸትና ክህደቶችን እያዥጎደጎደ ነው።አንገቴን ለካራ እሰጣለሁ፣ለውጭ ሃይሎች ጥቅምና ዛቻ አገሬን አሳልፌ አልሰጥም ሲል የነበረው ሰው አሁን በራሱ ልመናና ጥያቄ የአሜሪካኖችንና የምዕራብያውያንን ፍላጎት ተንበርክኮ ተቀብሏል።ጀፍሪ ፌልትማን የተባለውንም አገር አፍራሽ የአሜሪካ መንግሥት መልእክተኛ እባክህ ድረስልኝ ብሎ ለምኖ ያቀረበለትን የማስገደጃ ቅድመ ሁኔታ ሁሉ በመቀበል አገራችንንና ሕዝቧን መሳቂያ መሳለቂያ አድርጓታል። ሌሎቹንም አጋር መንግሥታት እንዲሁ ሸውዶ አሳዝኗቸዋል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ያለአጋር አስቀርቷታል።አሜሪካኖቹ በነጠላ የቀረችዋን አገራችንን በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት በተደጋጋሚ አንስተውት ግን በወዳጅ ተባባሪ መንግሥታት ጥረትና

ትግል ያልተደፈረው አገራዊ ህልውና አሁን የአብይ አህመድ መርመጥመጥና እጅ መስጠት ለሚፈልጉት ውሳኔ በር የከፈተላቸው ሲሆን ካለምንም ተቃውሞ አገራችን ካሳ ከፋይና እራሱንም ቢሆን ላቀረቡበት የዘር ማጥፋት (ጀኖሳይድ)ወንጀል ክስ ተጋልጦ ለሄጉ እስርቤት የሚዳርገው ይሆናል፤ነጥሎ መምታት ማለት እንዲህ ነው።ምናልባትም ካዘኑለት በሌላ አገር የመኖር ዕድል ሊያመቻቹለት ይችሉ ይሆናል። ያም ቢሆን ከወያኔ ጥቃት የሚያድነው አይሆንም።

ያልበሰለው፣ ከአድር ባዮቹና ከራሱ እይታና ፍላጎት ውጭ የሕዝቡን ጥያቄ ያላዳመጠው የአብይ እጣ ፈንታ በብዙ ውስብስብ መዳረሻዎች የተከበበ ሲሆን በአብዛኛው ግን  እግዜር ካቀለለለት ከአልበሽርና ከላይቤሪያው ወንጀለኛ መሪ ከቻርለስ ቴለር  ጋር  በእስር ቤት ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ዳማና ካርታ መጫወት ይሆናል።ከሁሉም ቀላሉ ግን በአነጎቹ የእርስ በርስ ሽኩቻና በቀል ሊሞት የሚችልበት ዕድሉ የጎላ ነው።በዚህ ሰው መዘዝ  የኢትዮጵያ ሕዝብም ለአፍሪካ አገሮች ምልክትና ፋና ወጊ የመሆኑን ታሪክ አጥቆሮታል።አብይ አህመድ ላይገፋበት ከዚምባብዌ መሪ ከነበሩት ከሮበርት ሙጋቤ እንደውርስ ነጥቆ ያሰማውን የአፍሪካውያኑን በዓለም የጸጥታው ምክርቤት ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት የሚለውን መቀስቀሻ መርሆ ከመዘዘና አፍሪካውያን ተቀብለው ካስተጋቡት በኋላ ነጮቹ የማይወዱት በመሆኑ ዳግም  ኢትዮጵያ እንኳንስ ለሌላው የአፍሪካ አገር ለራሷም ጥቅም ቢሆን እንዳትነሳ ለማድረግ ለዳግመኛ ጊዜ በወያኔ መዳፍ ሥር ወድቃ በአነግ እንዲሁም ተባባሪ ሃይሎች  የመበታተኗን አደጋ ከፍ እንዲል አድርጎታል።በዓለም አቀፍ ደረጃ በቃ የሚለውን የትግል መንፈስ ውሃ ቸልሶበታል።በዚህ ትግል ግንባር ቀደም ሆና የታገለችዋን የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዊት ጋዜጠኛ ሃርሜላ አረጋዊንና ቤተሰቧን አሳፍሯል፤ለወያኔ ጥቃትም አጋልጦ ሰጥቷቸዋል።እነሱም ያቀዱትን ያገር ውስጥ እንቅስቃሴ ሳይከውኑ ሞራላቸው ሁሉ ተሰብሮ ወደሚኖሩበት አገር እንዲመለሱ አድርጓቸዋል።ወያኔን በመታገሉ ጦር ሜዳ ደማቸውን ያፈሰሱትን ኤርትራውያንን ደም የውሻ ደም አድርጎታል፣ያለፈው የጠላትነት ስሜት ተወግዶ ለሰላማዊ ግንኙነት የተከፈተውን በር ጥርቅም አድርጎ ዘግቶታል።ዳግም  የጠላትነትን ስሜት ፈጥሯል።

የጥፋት ሃይሎቹን ፍላጎት ለመተግበር እንቅፋት የሆነባቸው የአማራው ማህበረሰብ ነው።ከጥፋት የተረፈው አማራ እራሱን በማደራጀት ከዳግመኛ ጥቃት ለመዳን በሚጥርበት ጊዜ ሁሉም የውጭና የውስጥ ጠላቶቹ ተባብረው ተነስተውበታል።ትጥቁን ለማስፈታት ዘመቻ ከፍተውበታል።

መንግሥት ነኝ ባዩ ቡድን በጭንቅ በተወጠረበት ሰዓት ጥላ ከለላ እንዲሆነው ሲዘምት የማረከውን መሣሪያ እንዲታጠቅ ፈቃድ ተሰጥቶት ነበር አሁን ግን የሥልጣን ወንበሩን ያረጋጋ ሲመስለው የክፉ ቀን መከታውን ለመበታተንና ለጥቃት እንዲጋለጥ የራሱንም መሣሪያ እንዲያስረክብ ተገዷል። መቋቋም ያልቻለውም መሳሪያ እያስረከበ ነው።

መሣሪያ መታጠቁ የመጣበትን ጠላት ለመቋቋም ሆኖ ሳለ ለማስረከብ ከሆነ መጀመሪያውኑ ባይታጠቀው ይሻለው ነበር፤ በሬዎቹን ሸጦ የገዛው መሳሪያ ቁም ነገር ሊሰራበት፣ህልውናውን ሊያስከብርበት፣እራሱንና ቤተሰቡን ሊከላከልበት፣ያገሩን ዳርድንበርና አንድነት ሊያስከብርበት እንጂ ተሸክሞ ለማድረስ አልነበረም።ግን ምን ያድርግ የራሱ መሪዎች ሲከዱትና ሲዘምቱበት ምርጫ አላገኘም።

አጼ ከህደቱ አብይ አህመድ በአማራው ክልል ወታደሮቹን ይዞ መግባቱ ተነግሯል።ይህም ለታይታና ለክብሩ ሳይሆን ብአዴን ከተባለው በድን ድርጅት ጋር በመመሳጠር የአማራውን መብት በመግፈፍ ከኖረበት መሬት ከራያና አዘቦ፣ከወልቃይትና ጠገሌ ተነቅሎ እንዲወጣና ለወያኔ እርቀሰላም ገጸበረከት ለማድረግ፣ ለዳግመኛ ጊዜ ተቃዋሚውንና የአማራውን ትግል በማፈን ፋኖንና ሕዝባዊ ሠራዊቱን

ትጥቁን በማስፈታት ለማጥቃት የተወሰነ እርምጃ መሆኑ በግልጽ ታይቷል።የጦርነቱም ተፈጸመ፣ የእርቀሰላም ጫጫታ የዚያ መንደርደሪያ መሆኑ ገሃድ እዬሆነ መጥቷል።

ይህንን ክህደት እነ ሳልሳዊ ራስፑቲን ዳንኤል ክብረት ግሩም ድንቅ ብስለትና ችሎታ የተመላበት አመራር ብለው ይጠሩታል።የሚገርመው ነገር ሳልሳዊ ራስፑቲን ዳንኤል ክብረት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ነኝ እያለ በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዩ በአጼ ክህደቱ አብይ አህመድ ዙፋን ስር መወሸቁና ለሚፈጽመው ጥፋትና ወንጀል ቡራኬ መስጠቱ ነው።ወይስ ተዋህዶ የሚለው አባባል በሳልሳዊ ራስፑቲን አመለካከት የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ ውህደት ማለት ይሆን? ለዚያ ሳይሆን አይቀርም ሰሞኑን በኦርቶዶክስና በፕሮቴስታንቱ መካከል በመስቀል አደባባይ የንብረት ይዞታ ዙሪያ በተነሳው ውዝግብ ላይ ድምጽ ከመስጠት የተቆጠበው።

ሳልሳዊ ራስፑቲን ዳንኤል ክብረትን ልንመክር የምንወደው ቢኖር እባክህ ወደ ቀልብህ ተመለስ፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶን ትምህርት አታርክስ፤ለአስርቱ ትዕዛዝ ተገዛ፣እራስን ከጥፋት አድን፣ለአገርና ለወገን በሚጠቅመው በሃይማኖቱ ሥራ አለያም በፖለቲካው መስክ ተሰማራ፣ሁለቱን አቀላቅለህ አታምታታ።ቤተመቅደስንና ቤተመንግሥትን ለይ። ወይ ሃይማኖተኛ አለያም ፖለቲከኛ ሆነህ አንድ መስመር ላይ ቁም።ደም ከሚያፈስ፣አገር ከሚያፈርስ ከጎሰኞች ድንኳን ውጣ፤ ለአገር አጥፊ ጎሰኞች መሣሪያ አትሁን።በያዝከው ከቀጠልክ የተሳፈርክበት የጎሰኞች መርከብ የማታ ማታ አንተንም ይዞ ይሰጥማል፣የአንተም አስከሬን እንደቀዳማዊ ራስፑቲን ከውሃ ውስጥ ተጠልፎ ይወጣል። ወይም እንደ አገርህ ዳግማዊ እራስፑቲን እንደ አባ ሃና የጥይት እራት ትሆናለህ።ምርጫው ያንተ ነው።

ሌሎቹም ምሑር ነን ባይ አሸርጋጆች ከምታደርጉት የጥፋት ምክር ተቆጥባችሁ እንደሰው አስቡ፣ የትምህርትና የእውቀት ደረጃችሁን የመፍትሔና የዘዴ ፋኖስ እንጂ የእንጀራ መብሊያ ሞሶብ አታድርጉት።ለእውነትና ስለእውነት መስክሩ፤እራሳችሁን የሃቅ ጠበቆች፣ለሌላው የአድርባይነት ሳይሆን የስነምግባርና ፣የጀግንነት ተምሳሌት አድርጉ።

ሌላው ኢትዮጵያዊም ህወሃት፣አህዴድና አነግ ከውጭ ጠላቶች ጋር ተባብረው በጣምራ የሚሰነዝሩትን ጥቃትና አገር የማፍረስ ሴራ በዝምታ ማለፍ አይገባም፤ በመነሳሳት ላይ ያሉትን አሰባስቦ ብሔራዊ አገር ወዳድ ሃይል መስርቶ ለመመከት ጊዜው አሁን ነው።አስፈላጊውን የስንቅና ትጥቅ በማሟላት፣ የፖለቲካ እራእይ ነድፎ ለመታገል ሁሉም አገር ወዳድ እንደየችሎታው ይሰለፍ።በጉልበቱ፣በእውቀቱ፣ በገንዘቡ መረባረቢያው ጊዜ አሁን ነው።ሌሎቹ እየዘረፉም እዬተረዱም የዚያ ባለቤት ሆነዋል።ብዙ ሆነህ ለጥቃቅኖቹ ጥቃት ሰለባ አትሁን።ቆፍጠን በል!!ሸሽተህ የማታመልጠው መከራ ተደግሶልሃልና ባለህበት ሆነህ መክተህ መልሰው፣ከቻልክም ተከታትለህ ድባቅ ምታው።ጠላቶችህ ሳይቀድሙህ ቅደማቸው።በውስጥህ ያለውን አውደልዳይና ሰላይ፣አድርባይ ከአድራጎቱ እንዲቆጠብ ምከረው፣እምቢ ካለም ፍረድበት።ጅብ ከሚበላህ ይልቅ በልተኸው ተቀደስ የሚለውን አባባል በተግባር ተርጉመው። መዘናጋት ብዙ ዋጋ አስከፍሏልና አትዘናጋ! እንደ ቆቅ ፈጣን እንደ ንስር ብልህና አስተዋይ ሁን!! የቅርቡን ብቻ ሳይሆን የሩቁንም ተመልከት!

ኢትዮጵያን ማዳን እራስን ማዳን ነው!!